# ኢህአፓ ለምን በአማራ ህዝብ ደም እና መከራ ላይ ለመቀለድ ደፈረ?

**Abeto Beyene, Thursday September 24, 2015**

**Source: https://www.facebook.com/profile.php?id=100009221610242&fref=nf**

==============

ኢትዮጵያን በጎሳ ፖለቲካ ከከፋፈሏት ቆሻሻ ትዉልድ ዉስጥ የሚመደበዉ ኢህአፓ: በሻዕቢያ አስተሳሰብ እየተዘወረ የአማራን ህዝብ በጨቋኝነት አስበይኖ: የኢትዮጵያን መሰረታዊ እሴቶች (ሌላዉ ቀርቶ ክርስትናዋ ሳይቀር) ረግሞና አስረግሞ በርካታ መከራና በደል ኢትዮጵያዉያን በኢትዮጵያዉያን ላይ እንዲፈጽሙ ያደረገ ድርጅት መሆኑ ግልጽ ነዉ:: ዋለልኝ ጸረ አማራ ጽንሰ ሀሳብ ጽፎ አማራዉን ከምድረ ገጽ ያስኣስጠፋ ሰዉ ነዉ:: ይሄ ሰዉ ኢህአፓ መሆኑን አትርሱ:: ኢትዮጵያ የብሄረሰቦች እስር ቤት በማለት ዜማ ያወጡትና አሳሪዉ ብሄረሰብ ደግሞ አማራ መሆኑን ከበሮ መትተዉ አማራዉን ያስጨፈጨፉት ኢህአፓዎች መሆናቸዉን አትርሱት:: እነ ታምራት ላይኔ እና ዛሬ ዋነኞቹ የብአዴን ቆሻሻ ሀላፊዎች ኢህአፓ መሆናቸዉን አትርሱት::

ይባስ ብሎ ኢህአፓ ሰሞኑን ያወጣዉ ተልካሻ እና በአማራ ህዝብ ጥላቻ የተሞላዉ መግለጫ ደግሞ ይሄ ፓርቲ የአማራ ህዝብ ጠላት ከመሆን ገና ያልጸዳ መሆኑን ግልጽ አድርጎ አሳይቶናል:: ኢህአፓ የአማራ ህዝብ በወያኔና በተባባሪዎቹ ሲታረድ እና ሲሰደድ አንድም ቀን መግልጫ ለማዉጣት ደፍሮ አያዉቅም ነበር:: ሆኖም አማሮች በጉሙዞች የደረሰባቸዉን መከራና የመበላት በደል ሞረሽ በድፍረት ለመላዉ አለም ስላሳወቀ ኢህአፓ የሚባለዉ የአማራ ጠላት ድርጅት ሞረሽን ሰሞኑን እየተሳደበ ነዉ:: በሞረሽ ላይም መግለጫ አዉጥቷል:: በተለይም ደብተራዉ " ፍኖተ ዲሞክራሲ የሚባሉ ልክሥክስ ሚዲያዎች በአማራ መገፋት ላይ ተሳልቀዋል::

የአማራ ብሶት ለምን ተነገረ ብሎ እስኪ እንዲህ መሆን ምን ይባላል? አማራን ለመናቅስ ይሄን ያህል ጉልበት ከዬት አገኙ?

ቤተ አማራዎች ተባበሩኝ እማ ! ይሄን ቆሻሻ ኢህአፓ የሚባል ፓርቲ ለኢትዮጵያ ህዝብ በተለይም ለአማራዉ ማንነቱን እናጋልጠዉ::